# ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር

KINIJIT NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS
(KNAASO)
766 Rock Creek Church Rd. NW Washington DC. 20010
Tel: (202) 541 0556 Fax: (202) 541-0557 Email: kinijitna@kinijitna.org


## ለመጨረሻው ድል በቁርጠኝነት መደራጀት አማረጭ የሌለው ነው

ሰኔ 10 2000

የሰሜን አሜሪካና ካናዳ የአንድነት (ቅንጅት) ድጋፍ ድርጅት ኅብረት

በመጀመሪያ ለመላው የዲሞክራሲና ፍትህ አፍቃሪ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዕንኳን ደስ ያላችሁ ለማለት እንወዳለን፡፡ በዓይነቱ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመሠረተው አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በሰላማዊ ትግሉ መንገድ ጸንቶ በመጓዝ ለሕዝባችንና ለአገራችን የማይቀለበስ ለውጥ ለማምጣት የሚያደርገውን መስዋዕትነት እያደነቅን እዚህ ደረጃ በመድረሱ የተሰማንን ደስታ ስንገልጽ ድጋፋችን ወደፊትም እንደሚቀጥል በማረጋገጥ ነው፡፡

የአንድነት ፓርቲ የግዜውን አደገኛ የፖለቲካ ቀውስ ለማስወገድ እንደዚሁም የነገይቱን ኢትዮጵያ አንድነትና ህልውና ለማረጋገጥ የሰላማዊ ትግል ስልት የሚከተል በመሆኑ ከግብ መድረሱ አይቀሬ ነው፡፡

በፖለታካና በኢኮኖሚ ቀውስ እጅና እግሩን ተጠፍሮ የሚገኘው ኢሕአደግ/ሕወሃት በአልሞት ባይ - ተጋዳይነት እየተንገዳገደ ባለበት በአሁኑ ወቅት ለይስሙላ ያወጣውን የራሱን ሕግ እንኳን ለማክበር አቅቶት በአንድነት ፓርቲ የምሥረታ ሂደት ላይ የፈጠረው ጫና ምን

ያህል በፍርሀት እንደተዋጠ ሲያሳይ በአንፃሩ ደግሞ የአንድነት ፓርቲ የሚከተለው ሰላማዊ መንገድ ትክክለኝነቱን የሚያረጋግጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በምርጫ 97 እናም ከዚያ በኋላ በአለው የትግል ሂደት ነጥረውና ጠርተው የወጡና ማንነታቸውንም በከፈሉት መስዋዕትነት የቀረፁት የሰላማዊ ትግሉ መሪዎቻችን ዛሬም እንደትናንትናው ማተባቸውን ሳይፈቱ፣ ከመንገዳቸውም አንዲት ጋት ዕንኳን ሳያፈገፍጉ ሕገ መንግስታዊ፣ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን በመጠቀም የመደራጀት ጥያቄን ከግብ ለማድረስ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆኑበትን ቁርጠኝነት የተሞላውን የዓላማ ፅናት በፅኑ የምንደግፍ ለመሆናችን ለማረጋገጥ እንወዳለን፡፡

ምርጫ 97 የአገራችንን የፓለቲካ እንቅስቃሴ ሕዝባችን በባለቤትነት የኔ ብሎ የያዘው መሆኑን እና ከዚህም በተጨማሪ ለመብቱ የተነሳውን ሕዝብ በተጠናና በተደራጀ መልኩ የመምራት አስፈላጊነት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ አጉልቶ አሳይቷል፡፡ ለለውጥ የተነሳሳ ሕዝብ ፍትሐዊ ጥያቄውን ይዞ ከተደራጀ እንደሚያሸንፍ የታወቀ ቢሆንም በትግል ሂደት ውስጥ ድርጅት በስሩ የተደራጀውን የሰው ኃይልና ጉልበት ለማሰማራት፣ ዓላማን አስጨብጦ ለግብ የሚያደርስ አስፈላጊ መሣሪያነቱ እውን ነው፡፡

እኛ በሰሜን አሜሪካና በካናዳ የምንገኝ የአንድነት ፓርቲ ደጋፊዎች በአሁኑ ወሳኝ ወቅት “ምን እናድርግ ?” ብለን ራሳችንን ስንጠይቅ የትግሉን አጀንዳ በተናጥል ማራመድ የማይቻል በመሆኑ ተደራጅቶ የድጋፍን አስተዋጾ ማበርከት አማራጭ የሌለው እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ እያንዳንዱ “ለነፃነቴ እኔም ድርሻዬን መክፈል አለብኝ” ብሎ ቆርጦ ከተነሳ አንድነቱም ሆነ ኅብረቱ ጠንካራ ሆኖ እንደሚገኝና የድሉን ቀን እንደሚያቃርበው ጥርጥር የለውም፡፡

የቅንጅት ዓላማና ራዕይ እንዲሁም የሰላማዊ ትግል ስልትን እንዳለ በመውረስ በምርጫ 97 የተገኘውን የሕዝብ ድጋፍ በድርጅታዊ ብቃት በማስተናገድ ሕዝባችንንና አገራችንን ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማሸጋገር ከኢሕአደግ/ሕወሃት አገዛዝ ጋር በግንባር ተፋጠው ለሚገኙት የሕዝብ ልጆች ያለንን ድጋፍ በተግባር ለማሳየት ቆርጠን መነሳሳት የዜግነት ግዴታችን ሊሆን ይገባል፡፡

በሰኔ 1997 የቅንጅት አባላት፣ ደጋፊዎችና ነጻነት የጠማው የኢትዮጵያ ሕዝብ የከፈሉት መሰዋዕትነት ፍሬ አፍረቶ በቆራጥነት ብዙዎች ዳግመኛ በመነሳሳት ባሉበት በአሁኑ ወቅት ከዳር ሆነን ከንፈር በመምጠጥ ከትግሉ ሸሽተን የምናፈሰው የአዞ እምባ አይኖርም፡፡

በመጨረሻም የአንድነት ፓርቲ ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚያደርገውን ጥረት ወደድልና ግብ ለማድረስ የሚያስችለውን የመደራጀት ጥያቄ እየመለሰ ባለበት በአሁኑ ወቅት፣ በመላው ዓለም የምትገኙ ኢትዮጵያዊያን የአንድነት ፓርቲን በሞራል፣ በገንዘብ፣ በዕውቀት ለመደገፍ በአንድነት ድጋፍ ድርጅቶች ሥር እንድትሰባሰቡ ስንጠይቅ የድጋፍ ድርጅቶች በሌሉበት ቦታዎች የምትገኙት ደግሞ የድጋፍ ድርጅቶችን በመመሥረት የትግሉን ባለቤትነት እንድትቀላቀሉ ጥሪ እናደርጋለን፡፡

ለዕብሪትና ለማን አለብኝነት ምላሻችን በቁርጠኝነት መደራጀት ነው!

የሰሜን አሜሪካ ቅንጅት ድጋፍ ማኅበር የካናዳ ቅንጅት ካውንስል